# ትንቢተ ሚክያስ

1 በይሁዳ ነገሥታት በኢዮአታም፣ በአ
ካዝና በሕዝቅያስ ዘመን ወደ ሞሬታ
ዊው ወደ ሚክያስ የመጣው የእግዚአብሔር
ቃል፣ ስለ ሰማርያና ስለ ኢየሩሳሌም ያየው
ራእይ ይህ ነው፤

2 እናንተ አሕዛብ ሆይ፤ ሁላችሁም ስሙ፤
ምድር ሆይ፤ በውስጧም የምትኖሩ
ሁሉ አድምጡ፤
ጌታ ከቅዱስ መቅደሱ፣
ልዑል እግዚአብሔር በእናንተ ላይ
ይመሰክርባችኋል።

## በሰማርያና በኢየሩሳሌም ላይ የተላለፈ ፍርድ

3 እነሆ፤ እግዚአብሔር ከመኖሪያ ስፍራው
ይመጣል፤
ወርዶም በምድር ከፍታዎች ላይ
ይራመዳል።
4 ተራሮች ከሥሩ ይቀልጣሉ፤
ሸለቆዎችም ይሰነጠቃሉ፤
በእሳት ፊት እንዳለ ሰም፣
በገደል ላይ እንደሚወርድ ፈሳሽ ይሆናሉ።
5 ይህ ሁሉ የሚሆነው ስለ ያዕቆብ በደል፣
ስለ እስራኤልም ቤት ኀጢአት ነው።
የያዕቆብ በደል ምንድን ነው?
ሰማርያ አይደለችምን?
የይሁዳስ የኰረብታ መስገጃ ምንድን ነው?
ኢየሩሳሌም አይደለችምን?

6 "ስለዚህ ሰማርያን የፍርስራሽ ክምር፣
ወይን የሚተከልባትም ስፍራ
አደርጋታለሁ፤
ድንጋዮቿን ወደ ሸለቆ አወርዳለሁ፤
መሠረቷንም ባዶ አደርጋለሁ።
7 ጣዖቶችዋ ሁሉ ይሰባበራሉ፤
ለቤተ መቅደሷ የቀረበው ገጸ በረከት
በእሳት ይቃጠላል፤
ምስሎችዋን ሁሉ እደመስሳለሁ፤
ገጸ በረከቷን በዝሙት አዳሪነት
እንደ ሰበሰበች ሁሉ፣
አሁንም ገጸ በረከትዋ የዝሙት
አዳሪነት ዋጋ መቀበያ ይሆናል።

## ልቅሶና ሐዘን

8 በዚህ ምክንያት አለቅሳለሁ፤ ዋይ ዋይም
እላለሁ፤
ባዶ እግሬንና ዕርቃኔን እሄዳለሁ፤
እንደ ቀበሮ አላዝናለሁ፤
እንደ ጉጉትም አቃስታለሁ።

9 ቍስሏ የማይሽር ነውና፤
ለይሁዳ ተርፎአል፤
እስከ ሕዝቤ መግቢያ በር፣
እስከ ኢየሩሳሌም እንኳ ደርሶአል።
10 በጌት[ሀ] አታውሩት፤
ከቶም አታልቅሱ[ለ]፤
በቤትዓፍራ[ሐ]፣
በትቢያ ላይ ተንከባለሉ።
11 እናንት በሻፊር[መ] የምትኖሩ፣
ዕርቃናችሁን ሆናችሁ በኀፍረት
ዕለፉ፤
በጸዓናን[ሠ] የሚኖሩ
ከዚያ አይወጡም፤
ቤትዔጼል በሐዘን ላይ ናት፤
ለእናንተም መጠጊያ ልትሆን
አትችልም።
12 ከመከራው መገላገልን በመሻት፣
በማሮት[ረ] የሚኖሩ በሥቃይ
ይወራጫሉ፤
እስከ ኢየሩሳሌም በር ሳይቀር፣
ክፉ ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ
መጥቶአልና።
13 እናንት በለኪሶ[ሰ] የምትኖሩ፣
ፈረሶችን ከሠረገላው ጋር አያይዙ፤
ለጽዮን ሴት ልጅ፣
የኀጢአት መጀመሪያ እናንት
ነበራችሁ፤
የእስራኤል በደል
በእናንተ ዘንድ ተገኝቶአልና።
14 ስለዚህ እናንተ ለሞሬሼትጌት፣
ማጫ ትሰጣላችሁ፤
የአክዚብ[ሸ] ከተማ፣
ለእስራኤል ነገሥታት መታለያ
ትሆናለች።
15 እናንት በመሪሳ[ቀ] የምትኖሩ
ድል አድራጊ አመጣባችኋለሁ፤
ያ የእስራኤል ክብር የሆነው
ወደ ዓዱላም ይመጣል።

[ሀ]10 'ጌት' የሚለው ቃል በዕብራይስጡ 'አውራ' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ አነባበብ አለው። [ለ]10 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ሲስማማ፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ግን 'በአኮ ላይ አታልቅሱ' ይላል። 'በአኮ' የሚለው የዕብራይስጡ ቃል 'አለቀሰ' ከሚለው የዕብራይስጡ ቃል ጋር ተመሳሳይ አነባበብ አለው። [ሐ]10 'ቤት ዓፍራ' ትርጒሙ 'የትቢያ ቤት' ማለት ነው።[መ]11 'ሻር' ትርጒሙ አስደሳች ማለት ነው። [ሠ]11 'ጻዓናን' የሚለው ቃል በዕብራይስጡ 'ውጣ' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ አነባበብ አለው። [ረ]12 'ማሮት' የሚለው ቃል በዕብራይስጡ 'መራራ' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ አነባበብ አለው። [ሰ]13 'ለኪሶ' የሚለው ቃል በዕብራይስጡ ቡድን ከሚለው ጋር ተመሳሳይ አነባበብ አለው። [ሸ]14 'አክዚብ' ትርጒሙ አታላይ/ማታለል ማለት ነው። [ቀ]15 'መሪሳ' የሚለው ቃል በዕብራይስጡ 'ድል አድራጊ' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ አነባበብ አለው።

1፥1 ቈ14፤ 1ዜና3፥12፡13፤ ኢሳ1፥1፤ ኤር26፥18፤ሆሴ1፥1
1፥2 ዘፍ31፥50፤ ዘዳ4፥26፤32፥1፤ መዝ11፥4፤50፥7፤ ኢሳ1፥2፤ኤር6፥19
1፥3 ኢሳ18፥4፤ 64፥1፤አሞ4፥13
1፥4 ዘኍ16፥31፤ ኢዮ9፥5፤መዝ46፥2፤ ናሆ1፥5
1፥5 አሞ8፥14
1፥6 ዘዳ20፥6፤ ሕዝ13፥14፤አሞ5፥11
1፥7 ዘፀ32፥20፤ ዘዳ9፥21፤23፥17-18፤ ሕዝ6፥6
1፥8 ኢሳ15፥3፤ 20፥2
1፥9 2ነገ18፥13፤ ኢሳ3፥26፤ ኤር10፥19፤46፥11
1፥11 ሕዝ23፥29
1፥12 ኤር14፥19፤ 40፥2
1፥13 ኢሱ10፥3፤ መዝ9፥14
1፥14 ቈ1፤ ኢሱ15፥44፤ 2ነገ16፥8፤ ኤር15፥18
1፥15 ኢሱ12፥15፤ 15፥44

16ደስ ለምትሰኙባቸው ልጆቻችሁ፣
በሐዘን ራሳችሁን ተላጩ፤
ራሳችሁን እንደ አሞራ ራስ ተመለጡት፤
ከእናንተ በምርኮ ይወሰዳሉና።

## የእግዚአብሔርና የሰው ዕቅድ

2 ክፉ ለመሥራት ለሚያቅዱ፣
በመኝታቸው ሳሉ ተንኰል
ለሚያውጠነጥኑ ወዮላቸው!
ሲነጋ በማለዳ ይፈጽሙታል፤
የሚያደርጉበት ኀይል በእጃቸው
ነውና።
2ዕርሻ ይመኛሉ፤ ይይዙታልም፤
ቤት ይመኛሉ፤ ይወስዱታልም፤
የሰውን ቤት፣
የባልንጀራን ርስት አታልለው ይወስዳሉ።
3ስለዚህ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

"እነሆ፤ በዚያ ሕዝብ ላይ ጥፋት ላመጣ
ዐቅጃለሁ፤
ከዚህም ለማምለጥ አትችሉም።
ከእንግዲህ በትዕቢት አትመላለሱም፤
የመከራ ጊዜ ይሆናልና።
4በዚያ ቀን ሰዎች ይሣለቁባችኋል፤
በሐዘን እንጕርጕሮ እንዲህ እያሉ
ያፌዙባችኋል፤
'እኛ ፈጽሞ ጠፍተናል፤
የወገኔ ርስት ተከፋፍሎአል።
ከእኔ ነጥቆ ወስዶ፣
ዕርሻዎቻችንን ላሸነፉን አከፋፈለ።'

5ስለዚህ *በእግዚአብሔር* ጉባኤ ውስጥ፣
መሬት በዕጣ የሚያካፍል ማንም
አይኖርም።

## ሐሰተኞች ነቢያት

6ነቢያቶቻቸው፣ "ትንቢት አትናገሩብን፤
ስለ እነዚህ ነገሮች ትንቢት አትናገር፤
ውርደት አይደርስብንም" ይላሉ።
7የያዕቆብ ቤት ሆይ፤ እንዲህ ሊባል ይገባልን?
"*የእግዚአብሔር መንፈስ የማይታገሥ* ነውን?
እንዲህ ያሉት ነገሮችንስ ያደርጋልን?"

"መንገዱ ቀና ለሆነ፣
ቃሌ መልካም አያደርግምን?
8በመጨረሻ በሕዝቤ ላይ ጠላት ሆናችሁ
ተነሣችሁ፤
የጦርነት ሐሳብ ሳይኖራቸው፣
በሰላም ከሚያልፉ ሰዎች ላይ፣
ማለፊያ መጐናጸፊያ ገፈፋችሁ።
9ከሚወዱት ቤታቸው፣
የሕዝቤን ሴቶች አስወጣችኋቸው፤
ክብሬን ከልጆቻቸው፣
ለዘላለም ወሰዳችሁ።
10ተነሡና፤ ከዚያ ሂዱ፤
ይህ ማረፊያ ቦታችሁ አይደለምና፤
ምክንያቱም ረክሶአል፤
ክፉኛም ተበላሽቶአል።
11ሐሰተኛና አታላይ ሰው መጥቶ፣
'ስለ ብዙ የወይን ጠጅና ስለሚያሰክር
መጠጥ ትንቢት እነግራችኋለሁ' ቢል፣
ለዚህ ሕዝብ ተቀባይነት ያለው ነቢይ
ይሆናል።

## የትድግና ተስፋ

12"ያዕቆብ ሆይ፤ በርግጥ ሁላችሁንም
እሰበስባለሁ፤
የእስራኤልንም ትሩፍ በአንድነት
አመጣለሁ፤
በጕረኖ ውስጥ እንዳሉ በጎች
በመሰማሪያ ላይ እንዳለ መንጋ
በአንድነት እሰበስባቸዋለሁ፤
ቦታውም በሕዝብ ይሞላል።
13የሚሰብረው ወጥቶ በፊታቸው ይሄዳል፤
እነርሱም በሩን በመስበር ወጥተው
ይሄዳሉ፤
*እግዚአብሔር* እየመራቸው፣
ንጉሣቸው ቀድሞአቸው ይሄዳል።

## መሪዎችና ነቢያት ተገሠጹ

3 ከዚያም እኔ እንዲህ አልሁ፤
"እናንት የያዕቆብ መሪዎች፤
እናንት የእስራኤል ቤት ገዦች ስሙ፤
ፍትሕን ማወቅ አይገባችሁምን?
2መልካሙን ጠላችሁ፤ ክፉውንም ወደዳችሁ፤
የሕዝቤን ቈዳ ገፈፋችሁ፤
ሥጋቸውንም ከዐጥንቶቻቸው ለያችሁ፤
3የሕዝቤን ሥጋ በላችሁ፤
ቈዳቸውን ገፈፋችሁ፤
ዐጥንቶቻቸውንም ሰባበራችሁ፤
በመጥበሻ እንደሚጠበስ፣
በድስት እንደሚቀቀል ሥጋ
ቈራረጣችኋቸው።
4እነርሱም ወደ *እግዚአብሔር* ይጮኻሉ፤
እርሱ ግን አይመልስላቸውም፤
ካደረጉት ክፋት የተነሣ፣
በዚያ ጊዜ ፊቱን ከእነርሱ ይሰውራል።

5*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

"ሕዝቤን የሚያስቱ ነቢያት፣
ሰው ሲያበላቸው፣ 'ሰላም አለ' ይላሉ፤
ሳያበላቸው ሲቀር ግን፣
ጦርነት ሊያውጁበት ይነሣሉ።
6ስለዚህ ሌሊቱ ያለ ራእይ፣
ጨለማውም ያለ ንግርት
ይመጣባችኋል፤
በነቢያት ላይ ፀሐይ ትጠልቅባቸዋለች፤
ቀኑም ይጨልምባቸዋል።

1፥16 ዘሌ13፥40፤ ዘዳ4፥27፤ ኢዮ1፥20፤ አሞ5፥27
2፥1 1ሳሙ29፥20፤ መዝ36፥4
2፥2 1ሳሙ8፥14፤ ምሳ30፥14፤ ኢሳ1፥23፤5፥8፤ ሕዝ46፥18
2፥3 ኢሳ2፥12፤ ኤር18፥11፤አሞ3፥1-2
2፥4 ዘሌ26፥31፤ ኤር4፥13፤6፥12
2፥5 ዘኍ34፥13፤ ዘዳ32፥13፤ኢሱ18፥4
2፥6 መዝ44፥13፤ ኤር18፥16፤19፥8፤ 25፥18፤29፥18፤ ሚክ6፥16
2፥7 መዝ15፥2፤ 84፥11፤119፥65
2፥9 ኤር10፥20
2፥10 ዘሌ18፥25-29፤ ዘዳ12፥9፤ መዝ106፥38-39፤ ሰቆ4፥15
2፥11 ዘሌ10፥9፤ 2ዜና36፥16፤ ኢሳ30፥10፤ኤር5፥31
2፥12 ነህ1፥9፤ ሚክ4፥7፤5፥7፤7፥18
2፥13 ኢሳ52፥12፤ 60፥11
3፥1 ኤር5፥5
3፥2 መዝ53፥4፤ ሕዝ22፥27
3፥3 ኢዮ24፥14፤ መዝ14፥4፤ ሕዝ11፥7፤24፥4-5፤ 34፥4
3፥4 ዘዳ1፥45፤ 31፥17፤1ሳሙ8፥18፤ ኢዮ15፥31፤ ኢሳ58፥4፤ ኤር11፥11፤ሕዝ8፥18
3፥5 ኢሳ3፥12፤ 9፥16፤53፥6፤ኤር4፥10
3፥6 ኢሳ8፥19-22፤ 29፥10፤ሕዝ7፥26፤ 12፥24፤አሞ8፥11

7ባለ ራእዮች ያፍራሉ፤
ንግርተኞችም ይዋረዳሉ፤
ሁሉም ፊታቸውን ይሸፍናሉ፤
ከእግዚአብሔር መልስ የለምና::”

8እኔ ግን፣
ለያዕቆብ በደሉን፣
ለእስራኤልም ኀጢአቱን እነግር ዘንድ
ኀይልን፣ በእግዚአብሔር መንፈስ፣
ፍትሕና ብርታት ተሞልቻለሁ::
9እናንት የያዕቆብ ቤት መሪዎች፣
እናንት የእስራኤል ቤት ገዦች፣
ፍትሕን የምትንቁ፤
ትክክለኛ የሆነውንም ነገር ሁሉ
የምታጣምሙ፤ ስሙ፤
10ጽዮንን ደም በማፍሰስ፣
ኢየሩሳሌምን በክፋት የምትገነቡ፤ ስሙ::
11መሪዎቿ በጉቦ ይፈርዳሉ፤
ካህናቷ ለዋጋ ሲሉ ያስተምራሉ፤
ነቢያቷም ለገንዘብ ሲሉ ይናገራሉ::
ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ
ተደግፈውም፣
“እግዚአብሔር በመካከላችን አይደለምን?
ምንም ዐይነት ክፉ ነገር አይደርስብንም”
ይላሉ::
12ስለዚህ በእናንተ ምክንያት፣
ጽዮን እንደ እርሻ ትታረሳለች፣
ኢየሩሳሌም የፍርስራሽ ክምር ትሆናለች፤
የቤተ መቅደሱም ኰረብታ ዐረም
የበቀለበት ጒብታ ይሆናል::

## የእግዚአብሔር ተራራ

4 በመጨረሻው ዘመን፣
የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተራራ፣
ከተራሮች ልቆ ይታያል፤
ከኰረብቶች በላይ ከፍ ይላል፤
ሕዝቦችም ወደ እርሱ ይጐርፋሉ::
2ብዙ አሕዛብ መጥተው እንዲህ ይላሉ፤
“ኑ፤ ወደ እግዚአብሔር ተራራ፣
ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንሂድ፤
በመንገዱ እንድንሄድ፣
መንገዱን ያስተምረናል::”
ሕግ ከጽዮን ይመጣል፤
የእግዚአብሔርም ቃል ከኢየሩሳሌም::
3እርሱ በብዙ ሕዝብ መካከል ይፈርዳል፤
በሩቅና በቅርብ ባሉ ኀያላን
መንግሥታት መካከል ያለውን ግጭት
ያቆማል፤
ሰይፋቸውን ማረሻ፣
ጦራቸውንም ማጭድ ያደርጉታል::
አንዱ መንግሥት በሌላው መንግሥት
ላይ ሰይፍ አያነሣም፤
ከእንግዲህም የጦርነት ትምህርት
አይማሩም::
4እያንዳንዱ ሰው በገዛ ወይኑ ሥር፣
ከገዛ በለሱም ሥር ይቀመጣል፤
የሚያስፈራቸው አይኖርም፤
የእግዚአብሔር ጸባኦት አፍ
ተናግሮአልና::
5አሕዛብ ሁሉ፣
በአማልክቶቻቸው ስም ይሄዳሉ፤
እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም እንሄዳለን::

## የእግዚአብሔር ዕቅድ

6እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“በዚያች ቀን ሽባውን እሰበስባለሁ፤
ስደተኞችንና ለሐዘን ያደረግኋቸውን፣
ወደ አንድ ቦታ አመጣለሁ::
7የሽባዎችን ትሩፍ፣
የተገፉትንም ብርቱ ሕዝብ አደርጋለሁ፤
ከዚያች ቀን አንሥቶ እስከ ዘላለም፣
እግዚአብሔር በጽዮን ተራራ በእነርሱ ላይ
ይነግሣል::
8አንተ የመንጋው መጠበቂያ ማማ ሆይ፤
የጽዮን ሴት ልጅ ዐምባ[በ] ሆይ፤
የቀድሞው ግዛትህ ይመለስልሃል፤
የመንግሥትም ሥልጣን ለኢየሩሳሌም
ሴት ልጅ ይሆናል::”

9አሁንስ እንደዚህ የምትጮኺው
ለምንድን ነው?
ንጉሥ የለሽምን?
ምጥ እንደ ያዛት ሴት የተጨነቅሽው፣
መካሪሽ ስለ ጠፋ ነውን?
10የጽዮን ሴት ልጅ ሆይ፤
ምጥ እንደ ያዛት ሴት ተጨነቂ፤
አሁንስ ከከተማ ወጥተሽ፣
በሜዳ ላይ መስፈር አለብሽና፤
ወደ ባቢሎን ትሄጃለሽ፣
በዚያ ከጠላት እጅ ትድኛለሽ፤
እግዚአብሔር በዚያ፣
ከጠላቶችሽ ይታደግሻል::

11አሁን ግን ብዙ አሕዛብ፣
በአንቺ ላይ ተሰብስበዋል፤
እነርሱም፣ “የረከሰች ትሁን፤
ዐይናችንም ጽዮንን መዘባበቻ
አድርጎ ይያት” ይላሉ::
12ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሐሳብ
አያውቁም፤
በአውድማ ላይ እንደ ነዶ
የሚሰበስባቸውን፣
የእርሱን ዕቅድ አያስተውሉም::

3፥7 ዘሌ13፥45፤ አስ6፥12፤ ኢሳ44፥25፤ ኤር6፥15፤ ሕዝ20፥3፤ሚክ7፥16
3፥8 ኢሳ57፥12፤ 61፥2
3፥9 መዝ58፥1-2፤ ኢሳ1፥23
3፥10 ኢሳ59፥7፤ ኤር22፥13:17፤ ሕዝ22፥27፤ ሚክ7፥2፤ናሆ3፥1፤ ዕን2፥12
3፥11 ዘፀ23፥8፤ ዘሌ19፥15፤ ኢሳ1፥23፤ 10፥20፤56፥11፤ ኤር6፥13፤7፥4፤ ሰቆ4፥13፤ሕዝ13፥9፤ 34፥2፤ሆሴ4፥8:18፤ ሚል2፥9
3፥12 ዘሌ26፥31፤ 2ነገ25፥9፤ ኢሳ6፥11፤ ኤር17፥3፤22፥6፤52፥13፤ ሰቆ5፥18፤ሕዝ5፥14
4፥1 መዝ22፥27፤ 48፥1፤86፥9፤ኤር3፥17፤ 31፥12፤ሕዝ17፥22፤ ዳን2፥35፤ዘካ8፥3
4፥2 ዘዳ18፥18፤ መዝ25፥8-9፤ 119፥171፤ ኢሳ54፥13፤ ኤር31፥6፤ ሕዝ20፥40፤ ዘካ2፥11፤14፥16
4፥3 መዝ46፥9፤ ኢሳ11፥4፤ኢል3፥10፤ ዘካ8፥20-22፤9፥10
4፥4 ዘሌ26፥6፤ 1ነገ4፥25፤ ኢሳ1፥20፤ ሕዝ39፥26
4፥5 ኢሱ24፥14-15፤ 2ነገ17፥29፤ ኢሳ26፥8፤ዘካ10፥12
4፥6 መዝ106፥47፤ ኤር31፥8፤ ሕዝ34፥13:16፤ 37፥21፤ሶፎ3፥19
4፥7 ዘፍ12፥2፤ ኢሳ2፥2፤ዳን2፥44፤ 7፥14፤ኢል2፥32፤ ሚክ2፥12፤ ሉቃ1፥33፤ራእ11፥15
4፥8 ኢሳ1፥26፤ ዘካ9፥9
4፥9 ዘፍ3፥16፤ ኤር8፥19፤ 30፥6፤48፥41
4፥10 ዘዳ21፥10፤ 2ነገ20፥18፤ ኢሳ43፥14፤48፥20
4፥11 ሰቆ2፥16፤ አብ1፥12፤ሚክ7፥8
4፥12 ዘፍ50፥20፤ ኢሳ55፥8፤ ሮሜ11፥33-34

[በ]8 ወይም ‘ኰረብታ’

13የጽዮን ልጅ ሆይ፤ ተነሥተሽ አበራዪ፤
የብረት ቀንድ እሰጥሻለሁና፤
የናስ ሰኰና እሰጥሻለሁ፤
አሕዛብንም ታደቂያቸዋለሽ።”
በግፍ ያግበሰበሱትን ትርፍ
*ለእግዚአብሔር*፣
ሀብታቸውንም ለምድር ሁሉ ጌታ
ታቀርቢያለሽ።

## ከቤተ ልሔም ገዥ እንደሚመጣ የተሰጠ ተስፋ

5 አንቺ የጭፍሮች ከተማ ሆይ፤
ጭፍሮችሽን አሰልፊ[ተ]፤
ከበባ ተደርጎብናልና፤
የእስራኤልን ገዥ፣
ጕንጬን በበትር ይመቱታል።

2“አንቺ ግን፣ ቤተ ልሔም ኤፍራታ
ሆይ፤
ከይሁዳ ነገዶች[ቸ] መካከል ትንሿ
ብትሆኚም፣
አመጣጡ[ኀ] ከጥንት፣
ከቀድሞ ዘመን[ነ] የሆነ፣
የእስራኤል ገዥ፣
ከአንቺ ይወጣልኛል።”

3ስለዚህ ወላዲቱ አምጣ እስክትገላገል ድረስ፣
እስራኤል ትተዋለች፤
የተቀሩት ወንድሞቹም፣
ተመልሰው ከእስራኤላውያን ጋር
ይቀላቀላሉ።

4*በእግዚአብሔር* ኀይል
በአምላኩ *በእግዚአብሔር* ስም ታላቅነት፣
ጸንቶ ይቆማል፤ መንጋውንም
ይጠብቃል።
በዚያን ጊዜ ኀያልነቱ እስከ ምድር ዳርቻ
ስለሚደርስ፣
ተደላድለው ይኖራሉ።
5እርሱም ሰላማቸው ይሆናል።

## ትድግናና ጥፋት

አሦራዊ ምድራችንን ሲወር፣
ምሽጎቻችንንም ጥሶ ሲገባ፣
ሰባት እረኞችን፣
እንዲያውም ስምንት አለቆችን
እናስነሣበታለን።
6የአሦርን ምድር በሰይፍ፣
የናምሩድን ምድር[ኘ] በተመዘዘ ሰይፍ ይገዙሉ[አ]፤
አሦራዊው ምድራችንን ሲወር፣
ዳር ድንበራችንን ሲደፍር፣
እርሱ ነጻ ያወጣናል።

7የያዕቆብ ትሩፍ፣
በብዙ አሕዛብ መካከል
*ከእግዚአብሔር* ዘንድ እንደሚወርድ
ጠል፣
በሣር ላይ እንደሚጥል ካፊያ፣
ሰውን እንደማይጠብቅ፣
የሰውንም ልጆች ተስፋ እንደማያደርግ
ሰው ይሆናል።
8በዱር አራዊት መካከል እንዳለ አንበሳ፣
በእግሩ እየጨፈላለቀ እንደሚሄድ፣
የሰበረውን ማንም ሊነጥቀው እንደማይችል፣
በበግ መንጋ መካከል እንዳለ፣
እንደ ደቦል አንበሳ ሁሉ፣
የያዕቆብም ትሩፍ፣ በአሕዛብ ዘንድ፣
በብዙም ሕዝብ መካከል እንደዚሁ ይሆናል።
9እጅህ በጠላቶችህ ላይ በድል አድራጊነት
ከፍ ከፍ ትላለች፤
ጠላቶችህም ሁሉ ይጠፋሉ።

10“በዚያን ጊዜ” ይላል *እግዚአብሔር*፤

“ፈረሶቻችሁን ከመካከላችሁ አጠፋለሁ፤
ሠረገሎቻችሁን እደመስሳለሁ።
11የምድራችሁን ከተሞች እደመስሳለሁ፤
ምሽጎቻችሁንም ሁሉ አፈርሳለሁ።
12ጥንቈላችሁን አጠፋለሁ፤
ከእንግዲህም አታሟርቱም።
13የተቀረጹ ምስሎቻችሁን፣
የማምለኪያ ዐምዶቻችሁንም ከመካከላችሁ
አጠፋለሁ፤
ከእንግዲህ ለእጃችሁ ሥራ
አትሰግዱም።
14የአሼራ ምስልን ዐምድ[ከ] ከመካከላችሁ
እነቅላለሁ፤
ከተሞቻችሁንም እደመስሳለሁ።
15ያልታዘዙኝን አሕዛብ፣
በቍጣና በመዓት እበቀላቸዋለሁ።”

## የእግዚአብሔር ክስ በእስራኤልን ላይ

6 *እግዚአብሔር* የሚለውን ስሙ፤
“ተነሡ፤ ጕዳያችሁን በተራሮችም፤
ፊት አቅርቡ፤
ኰረብቶች እናንተ የምትሉትን ይስሙ፤
2ተራሮች ሆይ፤ *የእግዚአብሔርን* ክስ
አድምጡ፤
እናንት የምድር ጽኑ መሠረቶችም፤
ስሙ፤
*እግዚአብሔር* ከሕዝቡ ጋር ክርክር አለውና፤
ከእስራኤልም ጋር ይፋረዳል።
3“ሕዝቤ ሆይ፤ ምን አድርጌሃለሁ?
ሸክም የሆንሁብህስ እንዴት ነው?
እስቲ መልስልኝ!
4ከግብፅ አወጣሁህ፤

[ተ]1 ወይም አንቺ የተቀጠርሽ ከተማ ሆይ፤ ቅጥርሽን አጥብቂ
[ቸ]2 ወይም ‘ገዦች’
[ነ]2 ወይም *ከቀድሞ ቀናት*
[ኀ]2 ዕብራይስጡ ‘አወጣጡ’ ይላል ወይም ‘ከዘላለም የሆነ’
[ኘ]6 ወይም ‘ናምሩድን በመግቢያው በር’
[አ]6 ወይም ‘ያፈርሳሉ’

4፥13 ኢሳ21፥10፤ 23፥18፤ዳን2፥44
5፥1 ሰቆ3፥30
5፥2 ዘፍ35፥16፤ 48፥7፤ዘኍ24፥19፤ 1ሳሙ13፥4፤ 2ሳሙ6፥21፤ 2ዜና7፥18፤ መዝ102፥25፤ ማቴ2፥6፤ዮሐ7፥42
5፥3 ኤር7፥29
5፥4 ኢሳ40፥11፤ 49፥9፤52፥13፤ ሕዝ34፥11-15፤23፤ ሚክ7፥14፤ሉቃ1፥32
5፥5 ኢሳ8፥7፤ 9፥6፤10፥24-27፤ ሉቃ2፥14፤
5፥6 ዘፍ10፥8፤ ናሆ2፥11-13፤ ሶፎ2፥13
5፥7 መዝ133፥3፤ ኢሳ44፥4፤ አሞ5፥15፤ሚክ2፥12
5፥8 ዘፍ49፥9፤ መዝ50፥22፤ ኢሳ5፥29፤ ሆሴ5፥14፤ ሚክ4፥13፤ዘካ10፥5
5፥9 መዝ10፥12
5፥10 ዘፀ15፥4፡19፤ ሆሴ14፥3፤ ሐጌ2፥22፤ዘካ9፥10
5፥11 ዘዳ29፥23፤ ኢሳ6፥11፤ ሰቆ2፥2፤ ሆሴ10፥14፤አሞ5፥9
5፥12 ዘዳ18፥10-12፤ ኢሳ2፥6፤8፥19
5፥13 ኢሳ2፥18፤ ሕዝ6፥9፤ ሆሴ10፥2፤ ናሆ1፥14፤ዘካ13፥2
5፥14 ዘፀ34፥13፤ መሳ3፥7፤2ነገ17፥10
6፥1 መዝ50፥1፤ ሕዝ6፥2
6፥2 ዘዳ32፥1፤ መዝ50፥7፤ ኢሳ3፥13፤ ኤር2፥9፤ሆሴ12፥2
6፥3 ኤር2፥5
6፥4 ዘፀ3፥10፤ 4፥16፤6፥6፤15፥20፤ ዘኍ33፥1፤ዘዳ7፥8፤ መዝ77፥20

ከባርነት ምድርም ተቤዠሁህ፤
እንዲመሩህ ሙሴን፣
አሮንንና ማርያምን ላክሁልህ።
5 ሕዝቤ ሆይ፤
የሞዓብ ንጉሥ ባላቅ የመከረውን፣
የቢዖር ልጅ በለዓም የመለሰለትንም
እስቲ አስቡ፤
*የእግዚአብሔርን* የጽድቅ ሥራ ታውቁ
ዘንድ፣
ከሰጢም እስከ ጌልገላ የተጓዛችሁትን
አስቡ።
6 ምን ይዤ *በእግዚአብሔር* ፊት
ልቅረብ፣
በልዑል አምላክ ፊት ልስገድ?
የሚቃጠለውን መሥዋዕት፣
ከአንድ ዓመት ጥጃ ጋር ይዤ በፊቱ
ልቅረብን?
7 በአንድ ሺህ አውራ በጎች፣
በዐሥር ሺህ የዘይት ፈሳሽ *እግዚአብሔር*
ደስ ይለዋልን?
ስለ በደሌ የበኵር ልጄን፣
ስለ ነፍሴም ኀጢአት የሆዴን ፍሬ
ላቅርብለትን?
8 ሰው ሆይ፤ መልካም የሆነውን
አሳይቶሃል፤
*እግዚአብሔር* ከአንተ የሚፈልገው
ምንድን ነው?
ፍትሕን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም
ትወድድ ዘንድ፣
በአምላክህም ፊት በትሕትና ትራመድ
ዘንድ አይደለምን?

## የእስራኤል በደልና ቅጣት

9 ስምህን መፍራት ጥበብ ነው፤
ስሙ! *እግዚአብሔር* ከተማዪቱን
እንዲህ እያለ ይጣራል፤
"በትሩን አስቡ፤ ያዘጋጀውም ማን እንደ
ሆነ አስታውሱ[ኸ]።
10 የክፋት ቤት ሆይ፤
በግፍ የተገኘ ሀብታችሁን፣
በሐሰተኛ መስፈሪያ የሰበሰባችሁትን
አስጸያፊ ነገር እረሳዋለሁን?
11 አባይ ሚዛን የያዘውን ሰው፣
ሐሰተኛ መመዘኛ በከረጢት
የቋጠረውን ንጹሕ ላድርገውን?
12 ባለጠጎቿ ግፈኞች፣
ሰዎችዋ ሐሰተኞች ናቸው፤
ምላሳቸውም አታላይ ናት።

13 ስለዚህ አንተን አጠፋሃለሁ፣
ከኀጢአትህ የተነሣ አፈራርስሃለሁ።
14 ትበላለህ፤ ነገር ግን አትጠግብም፤
ሆድህ እንዳለ ባዶውን[ሠ] ይቀራል፤

6፥5 ዘኍ22፥2፤ 25፥1፤ዘጸ11፥30፤ ኢሱ5፥9-10፤ መሳ5፥11፤1ሳሙ12፥7
6፥6 መዝ40፥6-8፤ 51፥16-17፤95፥2
6፥7 ዘሌ18፥21፤ 2ነገ3፥27፤ መዝ50፥8-10፤ ኢሳ1፥11፤40፥16፤ ሆሴ5፥6፤አሞ5፥22
6፥8 ዘፍ5፥22፤ ዘጸ10፥12-13፤ 1ሳሙ15፥22፤ 2ነገ22፥19፤ ኢሳ1፥17፤ 57፥15፤ኤር22፥3፤ ሆሴ6፥6፤ዘካ7፥9-10፤ ማቴ9፥13፤23፥23፤ ማር12፥33፤ሉቃ11፥42
6፥9 ዘፍ17፥1፤ ኢሳ11፥4
6፥10 ሕዝ45፥9-10፤ አሞ3፥10፤8፥4-6
6፥11 ዘሌ19፥36፤ ዘዳ25፥13
6፥12 መዝ35፥20፤ 116፥11፤ኢሳ1፥23፤ 3፥8፤ኤር9፥3
6፥13 ኢሳ1፥17፤ 6፥11
6፥14 ኢሳ9፥20፤ 30፥6፤ሆሴ4፥10
6፥15 ዘዳ28፥38፤ ኢዮ24፥11፤ ኤር12፥13፤አሞ5፥11፤ ሶፎ1፥13
6፥16 ዘዳ28፥37፤ 1ነገ16፥25፡29፡33፤ ኤር7፥24፤25፥9፤ 51፥51፤ሚክ2፥6
7፥1 መሐ2፥13
7፥2 መዝ10፥8፤ 12፥1፤ምሳ6፥17፤ ኢሳ3፥5፤ኤር2፥29፤ 5፥26፤ 8፥6፤ሚክ3፥10
7፥3 ዘፀ23፥8፤ ምሳ4፥16፤ ሕዝ22፥12
7፥4 ዘኍ33፥55፤ 2ሳሙ23፥6፤ ኢዮ31፥14፤ ኢሳ22፥5፤ ሕዝ2፥6፤ሆሴ9፥7
7፥5 ኤር9፥4
7፥6 ሕዝ22፥7፤ ማቴ10፥35-36፤ ማር13፥12

ታከማቻለህ፤ ነገር ግን አይጠራቀምልህም፤
የሰበሰብኸውን ለሰይፍ አደርገዋለሁና።
15 ትዘራለህ፤ ነገር ግን አታጭድም፤
የወይራ ዘይት ትጨምቃለህ፤ ነገር ግን
ዘይቱን አትቀባም፤
ወይንን ትቈርጣለህ፤ ነገር ግን የወይን ጠጅ
አትጠጣም።
16 የያምሪን ሥርዐት፣
የአክዓብን ቤት ልምድ ሁሉ የሙጥኝ
ብለሃል፤
ትውፊታቸውንም ተከትለሃል።
ስለዚህ አንተን ለውድመት፣
ሕዝብህን ለመዘባበቻ አሳልፌ እሰጣለሁ፤
አሕዛብም ይሣለቁብሃል[ዐ]።"

## የእስራኤል መከራ

7 ለእኔ ወዮልኝ!
የወይን ዕርሻ በሚቃረምበት ጊዜ
የበጋ ፍራፍሬ እንደሚለቅም ሰው
ሆኛለሁ፤
የሚበላ የወይን ዘለላ የለም፤
የምንጓጓለት፣ ቶሎ የሚደርሰው በለስም
አልተገኘም።
2 ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት ሰው ከምድር
ጠፍቶአል፤
አንድም እንኳ ቅን ሰው የለም፣
ሰው ሁሉ ደም ለማፍሰስ ያደባል፤
እያንዳንዱም ወንድሙን በመረብ
ያጠምዳል።
3 እጆቹ ክፉ ለማድረግ ሠልጥነዋል፤
ገዢ እጅ መንሻ ይፈልጋል፤
ፈራጁ ጉቦ ይቀበላል፤
ኀይለኞች ያሻቸውን ያስፈጽማሉ፤
ሁሉም አንድ ላይ ያሤራሉ።
4 ከእነርሱ ይሻላል የተባለው እንደ
አሜከላ፣
እጅግ ቀና የተባለውም እንደ ኵርንችት
ነው፤
የጠባቂዎቻችሁ ቀን ደርሶአል፤
የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን መጥቶአል፤
የሚሸበሩበትም ጊዜ አሁን ደርሶአል።
5 ባልንጀራህን አትመን፤
በጓደኛህም አትታመን፤
በዕቅፍህ ለምትተኛዋ እንኳ፣
ስለምትነግራት ቃል ተጠንቀቅ።
6 ወንድ ልጅ አባቱን ይንቃል፤

[ከ]14 አሼራ የተባለችው አምላክ ትእምርት ነው።
[ኸ]9 የዚህ ስንኝ የዕብራይስጡ ትርጒም በርግጠኝነት አይታወቅም።
[ሠ]14 የዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጒም በርግጠኝነት አይታወቅም።
[ዐ]16 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ሲስማማ የዕብራይስጡ ግን 'የሕዝቤን ስድብ ትሸከማለህ' ይላል
[ኸ]9 የዚህ ስንኝ የዕብራይስጡ ትርጒም በእርግጠኝነት አይታወቅም።
[ሠ]14 የዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጒም በርግጠኝነት አይታወቅም።
[ዐ]16 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ሲስማማ የዕብራይስጡ ግን 'የሕዝቤን ስድብ ትሸከማለህ' ይላል

ሴት ልጅ በእናቷ ላይ፤
ምራት በአማቷ ላይ ትነሣለች፤
የሰው ጠላቶች የገዛ ቤተ ሰዎቹ
ናቸውና።

[7]እኔ ግን *እግዚአብሔርን* ተስፋ አደርጋለሁ፤
አዳኜ የሆነውን አምላክ እጠብቃለሁ፤
አምላኬ ይሰማኛል።

## እስራኤል ትነሣለች

[8]ጠላቴ ሆይ፤ በእኔ ላይ በደረሰው ደስ
አይበልሽ!
ብወድቅም እንኳ እነሣለሁ፤
በጨለማ ብቀመጥ እንኳ፣
*እግዚአብሔር* ብርሃኔ ይሆናል።
[9]እርሱን ስለ በደልሁ፣
እስኪቆምልኝ
እስኪፈርድልኝም ድረስ፣
*የእግዚአብሔርን* ቍጣ እቀበላለሁ፤
እርሱ ወደ ብርሃን ያወጣኛል፤
እኔም ጽድቁን አያለሁ።
[10]ጠላቴም ታያለች፤
ኀፍረትንም ትከናነባለች፤
"አምላክህ *እግዚአብሔር* የት አለ?"
ያለችኝን፣
ዐይኖቼ ውድቀቷን ያያሉ፤
አሁንም እንኳ፣
እንደ መንገድ ጭቃ ትረገጣለች።

[11]ቅጥሮቻችሁን የምትሠሩበት፣
ድንበራችሁንም የምታሰፉበት ቀን
ይመጣል።
[12]በዚያ ቀን ሰዎች፣
ከአሦር እስከ ግብፅ ከተሞች፣
ከግብፅ እስከ ኤፍራጥስ፣
ከባሕር ወደ ባሕር፣
ከተራራ ወደ ተራራ ወደ እናንተ
ይመጣሉ።
[13]ከሥራቸው የተነሣ፣
በነዋሪዎቿ ምክንያት ምድር ባድማ
ትሆናለች።

7፥7 መዝ4፥3፤ 130፥5፤ኢሳ21፥8፤ 25፥9
7፥8 2ሳሙ22፥29፤ መዝ20፥8፤22፥17፤ 37፥24፤ምሳ24፥17፤ ኢሳ9፥2፤አሞ9፥11፤ ሚክ4፥11
7፥9 መዝ107፥10፤ 119፥154፤ ኢሳ46፥13፤ ሰቆ3፥39-40
7፥10 ሳሙ22፥43፤ ኢዮ40፥12፤ መዝ35፥26፤42፥3፤ ኢሳ5፥5፤51፥23፤ ዘካ10፥5
7፥11 ኢሳ54፥11፤ አሞ9፥11
7፥12 ኢሳ11፥11፤ 19፥23-25፤60፥4
7፥13 ኢሳ3፥10-1፤ ሕዝ12፥19፤33፥28-29
7፥14 መዝ23፥4፤ 28፥9፤95፥7፤ መሐ4፥1፤ኢሳ33፥9፤ ኤር50፥19፤ ሕዝ36፥11፤ሚክ5፥4
7፥15 ዘፀ3፥20፤ መዝ78፥12
7፥16 መሳ18፥19፤ ኢሳ26፥11
7፥17 ዘፍ3፥14፤ 2ሳሙ22፥46፤ ኢሳ25፥3፤59፥19
7፥18 ዘፀ8፥10፤ 34፥9፤1ሳሙ2፥2፤ 2ዜና6፥21፤30፥9፤ መዝ103፥8-13 ኢሳ43፥25፤54፥9፤ ኤር31፥20፤32፥41፤ 50፥20፤ሕዝ18፥23፤ ኢል2፥32፤ አሞ5፥15፤ሚክ2፥12፤ ዘካ3፥4
7፥19 ኢሳ43፥25፤ ኤር31፥34 ሉቃ1፥72

## ጸሎትና ውዳሴ

[14]ብቻቸውን በዱር ውስጥ፣
በለመለመ መስክ[ᐦ] የሚኖሩትን፣
የርስትህ መንጋ የሆኑትን፣
ሕዝብህን በበትርህ ጠብቅ፤
እንደ ቀድሞው ዘመን፣
በባሳንና በገለዓድ ይሰማሩ።

[15]"ከግብፅ እንደ ወጣህበት ዘመን ሁሉ፣
ታምራቴን አሳያቸዋለሁ።"

[16]አሕዛብ ያያሉ፣ ያፍራሉም፤
ኀይላቸውን ሁሉ ያጣሉ፤
አፋቸውን በእጃቸው ይይዛሉ፤
ጆሮአቸውም ትደነቍራለች።
[17]በደረታቸው እንደሚሳቡ ፍጥረታት፣
እንደ እባብም ትቢያ ይልሳሉ፤
ከዋሻቸው እየተንቀጠቀጡ ይወጣሉ፤
በፍርሀትም ወደ አምላካችን ወደ
*እግዚአብሔር* ይመለሳሉ፤
እናንተንም ይፈራሉ።
[18]የርስቱን ትሩፍ፣
ኀጢአት ይቅር የሚል፣ የሚምር
እንደ አንተ ያለ አምላክ ማነው?
ለዘላለም አትቈጣም፤
ነገር ግን ምሕረት በማድረግ ደስ
ይልሃል።
[19]ተመልሰህ ትራራልናለህ፤
ኀጢአታችንን በእግርህ ትረግጣለህ፤
በደላችንንም ሁሉ ወደ ጥልቁ ባሕር
ትጥላለህ።
[20]ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ
ለአባቶቻችን በመሐላ ቃል እንደ
ገባህላቸው፣
ለያዕቆብ ታማኝነትን፣
ለአብርሃምም ምሕረትን ታደርጋለህ።

ᐦ14 ወይም 'በቀርሜሎስ መካከል'